# ተነስ ፣ ሆ! በልና

አለቀ ደቀቀ ፣ አከተመ እንግዲህ
ወንበር ለመጋራት ፣ ማለት ወዲያ ወዲህ ፤
እስቲ ፣ አሁን እንኳን ፣ ይከፈት አይናችሁ
የምርጫ ግርግር ፣ እንዳለዋጣችሁ ።

ስለሆነም ዛሬ ፣ አይምሮ ግዙና
የህዝቡን ፍላጎት ፣ ብሶት አንግቡና ፤
የትግሉን ዘዴ ፣ ቅኝት ለውጣችሁ
በጽናት ታገሉ ፣ በድፍረት ወጥታችሁ ።

ካንዴም ፣ ሁለት ሶስቴ ፣ ሰው ከተሳሳተ
መንገዱ አላዋጣም ፣ በቃ ተከተተ ፤
ቆም ፣ ብሎ ማስተዋል ፣ የት ላይ ፣ እንደሳተ
አግባብነት አለው ፣ ከልብ ለጨመተ ።

መራራ ነው ትግል ፣ እረጅም አድካሚ
ውጣ ውርውድ ያለው ፣ አንዳንዴም አዝጋሚ
የቅርብና የሩቅ ፣ አስልቶ ተላሚ
ግቡን እስኪመታ ፣ ለድል ጸንቶ ቋሚ ።

ድክመት ጥንካሬን ፣ ባግባቡ መርምሮ
ስህተት ላለመድገም ፣ ካለፈው ተምሮ
የተበታተኑን ፣ ኃይሎች አስተባብሮ
በህብረት ለመስራት ፣ በአንድነት መክሮ
በስርአቱ መፍረስ ፣ አምኖበት አስምሮ
ትግሉን መቀጠል ነው ፣ የበለጠ አምርሮ
ከምን ግዜም በላይ ፣ በጽናት ጠንክሮ ።

አልጠፋም እሳቱ ፣ መቼ አመድ ሆነና
ይቆስቆስ ይቃጠል ፣ እረመጡ አለና
ይንቦግቦግ ሰደዱ ፣ ተነስ ፣ ሆ! በልና
ሕዝብ አቸናፊ ነው ፣ ድሉ የሱ ነውና ።

ታዛቢው … May 28, 2010